# በርጩማውም ጠፋ!

ከዓሣዬ

በምኞት ፈረሥ ጭኖ፣ ቁልቁል የጋለበኝ፣
በኣማላጅ ከመለስ፣ ሥልጣን ሊያስጨብጠኝ፣
እንደ ፊኛ ነፍቶ፣ ልቤን ያሣበጠኝ፣
ይኸውና ዛሬ፣
ፊኛውም ተንፍሶ፣ ዘርሮ ሲጥለኝ፣
በርጩማውም ጠፋ፣ ሕዝቡም እኔን ራቀኝ።

እስቲ መላ በሉ፣ ኣሁንስ ጨንቆኛል፣
ዙሪያው ገደል ሁኖ፣ ገደሉም ዞሮኛል፣
ሲመክሩኝ ማልሰማ፣ ሱሰኛ ሁኛለሁ፣
ዛሬም እንደ ትላንት፣
በምርጫ በርጩማ፣ ዳግም እቃጃለሁ፣
ለመጪው ኣምሥት ዓመት፣ ደጅ ጥናት ይዣለሁ።

ያደቆነ ሰይጣን፣ ኣልለቅህም ብሎኝ፣
ከሁለገብ ትግል፣ እንዳልደርስ ነጥሎኝ፣
ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከግራ ወደ ቀኝ፣
ከመለስ ጫማ ሥር፣ እያገላበጠኝ፣
እንዳይወድቅ  ድጋፉ፣ የታኮ አስገብቶኝ፣
ትግሉ እንዳይጠነክር፣ ጋሬጣው ሲያደርገኝ፣
እስቲ ዱዓ ኣድርጉ፣ ምለላም ያዙልኝ
በርጩማውም ጠፋ ፣ ሥልጣኑም እራቀኝ።

07/05/2010